የኢትዮጵያ ፌደራላዊ ዲሞክራሲያዊ ሪፐብሊክ

# ፌደራል ነጋሪት ጋዜጣ

# FEDERAL NEGARIT GAZETTE

## OF THE FEDERAL DEMOCRATIC REPUBLIC OF ETHIOPIA

ሰላሣኛ ዓመት ቁጥር ፴፰
አዲስ አበባ ሰኔ ፳፩ ቀን ፪ሺ፲፮ ዓ.ም

በኢትዮጵያ ፌደራላዊ ዲሞክራሲያዊ ሪፐብሊክ
የሕዝብ ተወካዮች ምክር ቤት ጠባቂነት የወጣ

30th Year No. 38
ADDIS ABABA 28th June, 2024

## ማውጫ

አዋጅ ቁጥር ፩ሺ፫፻፴፩/፪ሺ፲፮

ለቆላማ አካባቢዎች የኑሮ ማሻሻያ ፕሮጀክት ሁለተኛ ምዕራፍ ፕሮጀክት ማስፈፀሚያ የሚውል ብድር ከዓለም አቀፍ የልማት ማህበር ለማግኘት የተፈረመው የብድር ስምምነት ማፅደቂያ አዋጅ …………..ገጽ ፲፭ሺ፮፻፹፰

## Content

Proclamation No. 1331/2024

International Development Association Loan Agreement for financing Lowlands Livelihood Resilience Project- Phase II Ratification Proclamation …..……..........................Page 15688

### አዋጅ ቁጥር ፩ሺ፫፻፴፩/፪ሺ፲፮

### በኢትዮጵያ ፌደራላዊ ዲሞክራሲያዊ ሪፐብሊክ መንግስት እና በዓለም አቀፍ የልማት ማህበር መካከል የተደረገውን የብድር ስምምነት ለማፅደቅ የወጣ አዋጅ

ለቆላማ አካባቢዎች የኑሮ ማሻሻያ ፕሮጀክት ሁለተኛ ምዕራፍ ፕሮጀክት ማስፈፀሚያ የሚውል ሁለት መቶ ሃምሳ አምስት ሚሊዮን ሰባት መቶ ሺህ ኤስ ዲ አር (፪፻፶፭ ሚሊዮን ፯፻ ሺህ ኤስ.ዲ.አር) ብድር የሚያስገኘው የብድር ስምምነት በኢትዮጵያ ፌደራላዊ ዲሞክራሲያዊ ሪፐብሊክ መንግስት እና በዓለም አቀፍ የልማት ማህበር መካከል መጋቢት ፳፮ ቀን ፪ሺ፲፮ ዓ.ም በአዲስ አበባ የተፈረመ በመሆኑ፤

ይህንኑ ስምምነት የኢትዮጵያ ፌደራላዊ ዲሞክራሲያዊ ሪፐብሊክ የሕዝብ ተወካዮች ምክር ቤት በ ፳፱ኛ መደበኛ ስብሰባው ግንቦት ፳፪ ቀን ፪ሺ፲፮ ዓ.ም ያፀደቀው በመሆኑ፤

በኢትዮጵያ ፌደራላዊ ዲሞክራሲያዊ ሪፐብሊክ ሕገ መንግሥት አንቀጽ ፶፭(፩) እና (፲፪) መሠረት የሚከተለው ታውጇል፡፡

### PROCLAMATION NO. 1331/2024

### A PROCLAMATION TO RATIFY THE LOAN AGREEMENT BETWEEN THE GOVERNMENET OF THE FEDERAL DEMOCRATIC REPUBLIC OF ETHIOPIA AND INTERNATIONAL DEVELOPMENT ASSOCIATION

**WHEREAS**, the Loan Agreement, between the government of the Federal Democratic Republic of Ethiopia and International Development Association stipulating that International Development Association shall provide to the Federal Democratic Republic of Ethiopia a Loan an amount equivalent to Two Hundred and Fifty-Five Million Seven Hundred Thousand Special Drawing Rights (SDR 255,700,000) for Lowlands Livelihood Resilience Project- Phase II, was signed in Addis Ababa on 4th day of April, 2024;

**WHEREAS**, the House of Peoples' Representatives of the Federal Democratic Republic of Ethiopia has ratified the said Agreement at its 29th regular session held on 30th day of May, 2024;

**NOW, THERFORE**, in accordance with Article 55 Sub-Articles (1) and (12) of the Constitution of the Federal Democratic Republic of Ethiopia , it is hereby proclaimed as follows:

**፩. አጭር ርዕስ**

“ለቆላማ አካባቢዎች የኑሮ ማሻሻያ ፕሮጀክት ሁለተኛ ምዕራፍ ፕሮጀክት ማስፈፀሚያ የሚውል ብድር ከዓለም አቀፍ የልማት ማህበር ለማግኘት የተፈረመው የብድር ስምምነት ማፅደቂያ አዋጅ ቁጥር ፩ሺ፫፻፴፩/፪ሺ፲፮" ተብሎ ሊጠቀስ ይችላል፡፡

**፪. የስምምነቱ መፅደቅ**

በኢትዮጵያ ፌደራላዊ ዲሞክራሲያዊ ሪፐብሊክ መንግስት እና በዓለም አቀፍ የልማት ማህበር መካከል መጋቢት ፳፮ ቀን ፪ሺ፲፮ ዓ.ም በአዲስ አበባ የተፈረመው የብድር ስምምነት ቁጥር 7519-ET በዚህ አዋጅ ፀድቋል፡፡

**፫. የገንዘብ ሚኒስቴር ሥልጣን**

የገንዘብ ሚኒስቴር በብድር ስምምነቱ የተገኘውን ሁለት መቶ ሃምሳ አምስት ሚሊዮን ሰባት መቶ ሺህ ኤስ ዲ አር (፪፻፶፭ ሚሊዮን ፯፻ ሺህ ኤስ.ዲ.አር) በብድር ስምምነቱ በተመለከቱት ሁኔታዎች መሠረት በሥራ ላይ እንዲውል ለማድረግ በዚህ አዋጅ ሥልጣን ተሰጥቶታል፡፡

**፬. አዋጁ የሚፀናበት ጊዜ**

ይህ አዋጅ በፌደራል ነጋሪት ጋዜጣ ታትሞ ከወጣበት ቀን ጀምሮ የፀና ይሆናል፡፡

**አዲስ አበባ ሰኔ ፳፩ ቀን ፪ሺ፲፮ ዓ.ም**

**ሳህለወርቅ ዘውዴ**

**የኢትዮጵያ ፌዴራላዊ ዲሞክራሲያዊ ሪፐብሊክ ፕሬዚዳንት**



**1. Short Title**

This Proclamation may be cited as the “International Development Association Loan Agreement for financing Lowlands Livelihood Resilience Project- Phase II Ratification Proclamation No. 1331/2024”.

**2. Ratification of the Agreement**

The Loan Agreement Number 7519-ET signed in Addis Ababa on 4th day of April, 2024 between the government of the Federal Democratic Republic of Ethiopia and International Development Association is hereby ratified.

**3. Power of the Ministry of Finance**

The Ministry of Finance is hereby empowered to undertake all acts necessary for the utilization of the Loan an amount equivalent to Two Hundred And Fifty-Five Million Seven Hundred Thousand Special Drawing Rights (SDR 255,700,000) in accordance with the terms and conditions set forth in the Loan Agreement.

**4. Effective Date**

This Proclamation shall enter into force up on its publication in the Federal Negarit Gazettee.

**Done at Addis Ababa, on this 28th day of June, 2024.**

**SAHLEWORK ZEWDE**

**PRESIDENT OF THE FEDERAL DEMOCRATICREPUBLIC OF ETHIOPIA**